## 35ቱ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት

47.የማቴዎስ ወንጌል
48. የማርቆስ ወንጌል
49. የሉቃስ ወንጌል
50. የዮሐንስ ወንጌል
51. የሐዋርያት ሥራ(መጽሐፈ አብረክሲስ)
52. የሮሜ መልእክት
53. 1ኛ ቆሮንቶስ
54 2ኛ ቆሮንቶስ
55. የገላትያ መልእክት
56. የኤፌሶን መልእክት
57. የፊልጵስዩስ መልእክት
58 የቆላስይስ መልእክት
59. 1ኛ ተሰሎንቄ
60. 2ኛ ተሰሎንቄ
61 1ኛ ጢሞቴዎስ
62. 2ኛ ጢሞቴዎስ
63.የቲቶ መልእክት
64. የፊልሞና መልእክት
65. የዕብራውያን መልእክት
66. 1ኛ ጴጥሮስ
67. 2ኛ ጴጥሮስ
68. 1ኛ ዮሐንስ
69. 2ኛ ዮሐንስ
70. 3ኛ ዮሐንስ
71. የያዕቆብ መልእክት
72. የይሁዳ መልእክት
73. የዮሐንስ ራእይ
74. ሥርዓት ጽዮን ሲኖዶስ
75. ትእዛዝ ሲኖዶስ
76. ግጽው ሲኖዶስ
77. አብጥሊስ ሲኖዶስ
78.1ኛ መጽሐፈ ኪዳን
79. 2ኛ መጽሐፈ ኪዳን
80. ቀሌምንጦስ
81. ዲድስቅልያ

PDF Scanner Create

እንደዚሁም ሁሉ ከመጽሐፍ ቅዱስ መካከል የተወሰኑትን ብቻ ይዞ በመጓዝ «ሸክምን ስማቅሰል» የሚሞክር ካለ እንደጉደሎው እንሥራ የጥርጥር ማዕበል ከወዲያ ወዲህ እያማታው በሥጋም በነፍስም እንዳይጐዳ መጠንቀቅ አለበት።

ለመሆኑ አንዳንድ ድርጅቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉት ቅዱሳት መጻሕፍት ብዛት ከሰማንያ አሐዱ በታች ናቸው ለማለት እንደ ምክንያት የሚያነሷቸው ጥያቄዎች የትኞቹ ናቸው? እነዚህ ጥያቄዎች ሁለት ናቸው። እነርሱንም ከእነ ምላሻ ቸው ቀጥለን እንመልከት:-

1. «ከመጽሐፍ ቅዱስ ቁጥር ተራ ገብተው ከሚቆጠሩ ት መካከል አንዳንዶቹን መጽሐፈ ጦቢት፣ መጽሐፈ ዮዲት፣ መጽሐፈ ጥበብ፣ መጽሐፈ ሲራክ፣ መጽሐፈ መቃብያን፣ መጽሐፈ ባሮክ፣ ተረፈ ዳንኤል፣ ተረፈ ኤርምያስ፣ መጽሐፈ ሄኖክ፣ መጽሐፈ ኩፋሌ፣ መጽሐፈ ዕዝራ ሱቱኤልና ዮሴፍ ወልደ ኩርዮንን አይሁድ አልተረከቧቸውም ሰባው ሊቃናትም ብሉይ ኪዳንን ከዕብራይስጥ ወደ ጽርዕ ሲተረጉሙ አልተረጐሟቸውም። እኛ ደግሞ መጻሕፍቱን ያገኘነው ከእነርሱ በመሆኑ እነርሱ ካስረከቡን ውጭ እንዴት እንቀበላለን?» በማለት ይናገራሉ።

ምንም እንኳን አይሁድ እነዚህን መጻሕፍት ከሌሎች ጋር አብረው ያልያዟቸው ቢሆንም ከጊዜ በኋላ ግን ተገቢውን ቦታ ሰጥተዋቸዋል። አልተቀበሏቸውም ማለት ግን ፈጽሞ ስህተት ነው። ለዚህም ምስክር የሚሆነን ከክርስቶስ ልደት 534 ዓመት በፊት ዕዝራና አብረውት የነበሩት ነቢያት መጻሕፍቱን ሲያስባስቡ በዕብራይስጥ የተጻፉትን ብቻ ነበረ። በሌላ ቋንቋ የተጻፉት ሳይሰበሰቡ ቀርተዋል። ኋላም እንደ ዕዝራ ተሰሚነት ያለው ነቢይ ባለመነሣቱ ከእርሱ በኋላ የተጻፉት መጻሕፍት ተቀባይነት ቢቀነስም በአይሁድ ምሁራን ዘንድ ግን ክብር የተሰጣቸው ነበሩ።

ምክንያቱም ከጌታችን ልደት 284 ዓመት በፊት በበጥሊሞስ ዘመነ መንግሥት ሰባው ሊቃ ናት (ሰብዐ ሊቃ ናት) ከዕብራይስጥ ወደ ጽርዕ (የግሪክ ቋንቋ) የተተረጐሙት መጻሕ ፍት እነዚህን ማጠቃለሉ በቂ ማስረጃ ነው። ሰባው ሊቃናት አልተረጐሟቸውም የሚለው አመለካከት ግን ፈጽሞ ተቀባይነት የለውም። በ1950 ዓ.ም (እ.ኤ.አ) ግሪኮች ባሳተሙት መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መጽሐፈ ጦቢት፣መጽሐፈ ዮዲት፣ ከ1ኛ እስከ 3ኛ መቃብያን፣ አራተኛ መቃ ብያንን ጨምሮ ( ዮሴፍ ወልደ ኩርዮን ሳይሆን አይቀርም)፣ መጽሐፈ ጥበብ፣ መጽሐፈ ሲራክ እና መጽሐፈ ባሮክ ይገኙበታል።

PDF Scanner Create

